የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 21
ADDIS ABABA - 15th May, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፬/፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
ለሰባተኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ልማት መርሐ ግብር ማስፈፀሚያ ከኖርድባንከን ኤቢ. ተጨማሪ ብድር ለማግኘት የብድር ዋስትና ለመስጠት የተፈረመው የዋስትና ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፩ሺ፬፻፹፬

## CONTENTS

Proclamation No. 234/2001
Nordbanken AB Financial Agreement to Provide Additional Loan for Financing the 7th Telecommunications Development Programme Guaranteeing Agreement Ratification Proclamation ..... Page 1484

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፬/፲፱፻፺፫

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርድባንከን ኤቢ. መካከል የተደረገውን የዋስትና ውል ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሰባተኛው የቴሌኮሙኒኬሽን የልማት መርሐ ግብር ከፊል ማስፈጸሚያ የሚውል ፩፻፲፪ ሚሊዮን ፭፻ሺ (አንድ መቶ አሥራ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) ክሮነር ብድር ለማግኘት በኖርድባንከን እና በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን መካከል የተፈረመውንና የገንዘብ ሚኒስቴር ዋስትና የሰጠበትን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

ፕሮጀክቱን በታቀደው መሠረት ለማጠናቀቅ የሚያስፈል ገውን ተጨማሪ ሴክ ፲፪ ሚሊዮን (አሥራ ሁለት ሚሊዮን የስዊድን ክሮነር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒ ኬሽን ኮርፖሬሽን (ተበዳሪ)፣ ኖርድባንከን ኤቢ. (አበዳሪ) እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ዋስ) መካከል እ.ኤ.አ. ኦገስት ፳፪ ቀን ፪ሺ የተፈረመ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ በሪፐብሊክ ዋስትና ግዴታ የሚገባባቸው ስምምነቶች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

### PROCLAMATION NO. 234/2001

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE GUARANTEE AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND NORDBANKEN AB

WHEREAS, a Loan Agreement in the amount of 112,500,000 Swedish Kroner for partly financing the 7th Telecommmunications Development Programme signed between the Ethiopian Telecommunications Corporation and Nordbanken in which the Ministry of Finance has signed as Guarantor has been ratified by the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia at its session held on the 22nd, day of April, 1997;

WHEREAS, a Financial Agreement, between the Ethiopian Telecommunications Corporation (the ''Borrower''), Nordbanken AB (the ''Lender'') and the Federal Democratic Republic of Ethioppia (the ''Guarantor'') stipulating that Nordbanken AB provides to the Ethiopian Telecommunications Corporation additional twelve million Swedish Kroner (SEK 12,000,000) to be used for completing the Project as planned was signed on the 22nd day of August, 2000;

WHEREAS, agreements in which the Federal Democratic Republic of Ethiopia is a Guarantor have to be ratified prior to entry into force;

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

ይህንኑ የዋስትና ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለሰባተኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ልማት መርሐ ግብር ማስፈፀሚያ ከኖርድባንከን ኤቢ ተጨማሪ ብድር ለማግኘት የብድር ዋስትና ለመስጠት የተፈረመው የዋስትና ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፬/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኖርድባንከን ኤቢ (አበዳሪ) ፣ በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን (ተበዳሪ) ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ዋስ) መካከል እ·ኤ·አ· ኦገስት ፳፪ ቀን ፪ሺ የተፈረመው ስምምነት ነው።

፫· <u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ዋስ የሆነበትና በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፪ የተጠቀሰው ስምምነት ፀድቋል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Guarantee Agreement at its session held on the 15th day of May, 2001;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Nordbanken AB Financial Agreement to Provide Additional Loan for financing the 7th Telecommunications Development Programme Guaranteeing Agreement Ratification Proclamation No. 234/2001."

2. *Definition*

In this Proclamation "Financial Agreement" means the Agreement signed on the 22nd day of August, 2000, between the Nordbanken AB (Lender), the Ethiopian Telecommunications Corporation (Borrower) and the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Guarantor).

3. *Approval*

The Financial Agreement mentioned under Article 2 above, in which the Federal Democratic Republic of Ethiopia is a Guarantor is approved.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 15th day of May, 2001.

*Done at Addis Ababa this 15th day of May, 2001.*

*NEGASO GIDADA (DR.)*

*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE